ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies(FSS)

መጋቢት 2015 የፖሊሲ ፍሬ ኃሳቦች ቁጥር 47

# በኢትዮጵያ በተመረጡ የጨርቃ-ጨርቅ እና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች የሴት ቅጥር ሠራተኞች የሥራ ሁኔታ እና የተስተዋሉ ለውጦች

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ ነክ ምርምሮችን የሚያካሂድ ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው።

♣ ♣ ♣

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሠብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

♣ ♣ ♣

በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፤ በልማት ዙሪያ ውይይቶችንም ያካሂዳል።

♣ ♣ ♣

በርዕሱ ዙሪያ ኃሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜል አድራሻችን ላኩልን።

♣ ♣ ♣

ኢሜል፡ fss@ethionet.et

ድረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org

## መግቢያ

ሥራ አጥነት የኢትዮጵያ ከተሞች የኢኮኖሚ ችግር ሆኖ ለብዙ ጊዜ ቆይቷል፡፡ እ.ኤ.አ. በ2020 ዓ.ም. በማእከላዊ ስታትስቲካል ኤጀንሲ የተሰራው የከተማ ሥራ እና ሥራ አጥነት የዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየው የከተማ ሥራ አጥነት 18.7 በመቶ ደርሷል። የጥናት ዳሰሳው ሥራ መስራት ከሚችሉ ሴቶች መካከል 26.1 በመቶ የሚሆኑት ሥራ አጥ መሆናቸውን ያሳያል። ምንም እንኳን በኢ-መደበኛ ሴክተር ውስጥ ሴቶች (24 በመቶ) ከወንዶች (10 በመቶ) ጋር ሲወዳደር ተሳትፏቸው በልጦ ቢታይም፣ በቅርብ ጊዜያት ሴቶች መደበኛ ሴክተሩን በተሻለ ሁኔታ እየተቀላቀሉ ይገኛሉ። በአጠቃላይ የማኑፋክቸሪንግ ሴክተር በተለይም ደግሞ የጨርቃ- ጨርቅ ኢንዱስትሪው ለወጣቱ ሥራ የሚፈጥር ተደርጎ ይታያል።

ምንም እንኳን የጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት ሴክተር ለሴቶች የሥራ እድል እያመቻቸ ቢገኝም በተለይም ዝቅ ያለ ክህሎች በሚፈልጉ የስራ ዘርፎች ውስጥ እየሰሩ የሚገኙ ሴቶች የፆታ መድሎ፣ ያልተመጣጠነ ክፍያ እንዲሁም ደህንነት የጎደለው የሥራ ከባቢ እና የመሳሰሉት ተግዳሮቶች ሲገጥሟቸው ይታያል። ይህ ጥናት ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶችን እንዲሁም መስክ ላይ መሠረት ያደረጉ መረጃዎችን በመጠቀም በጨርቃ-ጨርቅ እና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሴቶችን የስራ ሁኔታ ለመዳሰስ ያለመ ነው።

## የጥናቱ ዘዴ

የጥናቱ አካሄድ ድብልቅ መሆኑን ተከትሎ አሃዛዊ እና አይነታዊ የትንተና ዘዴ ተተግብሯል፡፡ ለጥናቱ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ በዳሰሳ ጥናት፣ በቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ቃለ-መጠይቅ፣ የሰራተኞችን ህይወት በጥልቀት በተመለከተ ቃለ-መጠይቅ እንዲሁም የቡድን ውይይትን እና ምልከታዎችን በመጠቀም ተሰብስቧል። የተሰበሰበው የቁጥር መረጃ Statistical Package for Social Scientists (SPSS) በተሰኘ ሶፍትዌር አማካኝነት ተተንትኗል። በአይነታዊ ዘዴ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተጨምቀው እና ተቀንሰው በፈርጅ በፈርጁ ተቀምጠዋል። በመጀመሪያ መረጃ ለመሰብሰብ ቦሌ ለሚ እንዱስትሪ ፓርክ እና አዲስ የኢንዱስትሪ መንደር ተመርጠው የነበሩ ቢሆንም ጥናቱ በተካሄደበት ጊዜ ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ከኮሮና ወረርሽኝ ጋር በተገናኘ የውጪ ሰዎች ወደ ፓርኩ እንዳይገቡ የሚል እገዳ ስለጣለ ይህ ፓርክ በጥቃቅን እና መካከለኛ አልባሳት እኢንተርፕራይዝ ተተክቷል።

## የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

### በጨርቃ-ጨርቅ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የሚሰሩ የሴት ተቀጣሪዎች ሁኔታ

ለጥናቱ በተመረጡ የጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት ፋብሪካዎች ውስጥ የሚሠሩ ሴት ሠራተኞች ሲቀጠሩ 1280.86 ብር በወር ይከፈላቸዋል። ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት በፋብሪካዎች ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች በአማካይ 2066 ብር በወር ይከፈላቸው ነበር። በአዲስ ኢንዱስትሪ መንደር ውስጥ የሚሰሩ ሴቶች በዓመት የደመወዝ ጭማሪ በአማካይ 2.67 ሲሆን በጥቃቅንና መካከለኛ አልባሳት ኢንተርራይዝ 2.77 በመቶ ነበር። በፋብሪካዎቹ ውስጥ ለሴቶች የሚከፈለው ደመወዝ ሰራተኞቹ ያላቸውን የመሰረታዊ ፍላጎቶች ወጪ በቅጡ አይሸፍንም። ይህ ሁኔታ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ እየናረ በመጣው የዋጋ ግሽበት ተባብሷል።

በጨርቃ-ጨርቅ እና አልባሳት ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚሰሩ ሴቶች በበቂ ያለመከፈል ችግርን ከመቅረፍ አንፃር በመንግስት በኩል አስፈላጊው ጥረት ሲደረግ አይታይም። እንደውም መንግስት ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት በጣም ዝቅተኛ ደምወዝ ተከፋይ የጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት ፋብሪካ ሰራተኞች ያሉባት ሀገር መሆኗን በኩራት ሲናገር ይስተዋላል። ይህን በተመለከተ ከመንግስት በኩል አነስተኛ ክፍያን አለመወሰኑ እንደ አንድ ተግዳሮት ሆኖ ቆይቷል። የተሻሻለው የአሠሪና ሠራተና ጉዳይ አዋጅ አነስተኛ ደመወዝ የሀገሪቷን የኢኮኖሚ እድገት ባገናዘበ መልኩ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል። ነገር ግን የደመወዝ ቦርድ አሁንም አልተቋቋመም።

### በጨርቃ-ጨርቅ እና አልባሳት ፋብሪካዎች ውስጥ ያለው የጤና እና የስራ ቦታ ደህንነት ሁኔታ

በጥናቱ የተሳተፉ ሠራተኞች በሥራ ምክንያት የደረሰባቸው ከባድ ጉዳት የለም:: ሪፖርት የተደረጉት ጥቂት በሥራ ምክንያት የደረሱ አደጋዎች በመርፌ የመወጋት አደጋ እና ከዛ ጋር የተያያዘ ኢንፌክሽን ናቸው። በሥራ ምክንያት አደጋ በሚደርስበት ጊዜ እና አደጋዉም ቀላል ሲሆን ፣ፋብሪካዎቹ በሥራ ቦታ ባላቸው የመጀመሪያ ጊዜ አደጋ እረዳታ መስጫ ቁሳቁሶች ይጠቀማሉ። ነገር ግን አደጋው የከፋ ከሆነ ሰራተኞቹ ወደ ጤና ማእከላት ሄደው ይታከማሉ። ፋብሪካዎቹም የራሳቸው የሆነ የጤና ማእከላት ስለሌላቸው የሰራተኞቹን የመጓጓዣ እና የመታከሚያ ወጪ ይሸፍናሉ።

በሥራ ምክንያት ከሚደርሱ አደጋዎች ውጪ የፋብሪካዎቹ ሥራ በሴት ሠራተኞች ላይ ለተለያዩ የጤና ችግሮች እንደሚያጋልጥ ሰራተኞቹ ይናገራሉ። ከነዚህም ውስጥ ሴት ሰራተኞች ለበርካታ ሰዓታት ቆመው ከመስራታቸው ጋር በተገናኘ እግራቸው እንደሚያብጥ እና በዚህም ምክንያት ለኩላሊት ህመም እንደሚጋለጡ ይናገራሉ።

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁ የሠራተኞችን የጤና መድን የማግኘት መብት አይደነግግም። አዋጁ የሚያጠቃልለው በሥራ ላይ የሚከሰት አደጋን ብቻ ነው። ነገር ግን የኢትዮጵያ የ20 አመት የጤና እቅድ ሁሉም ዜጋ የጤና አገልግሎትን ያለምንም ችግር እንዲያገኝ መንግስት እየሰራ ስለሆነ፣ በፋብሪካ ውስጥ የሚሰሩ ሴት ሠራተኞችም በዚህ ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል።

### በጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የሚሰሩ ሴቶች የሚያገኙት ጥቅም እና የሚገጠሟቸው ተግዳሮቶች

በጥናቱ ውስጥ የተሳተፉ የጨርቃ-ጨርቅ እና አልባሳት ፋብሪካዎች ለሴቶች የስራ ዕድል መፍጠራቸው ጠቀሜታ አለው። በዳሰሳ ጥናት ከተሳተፉ ሴቶች መካከል 32 በመቶ የሚሆኑት በፋብሪካዎቹ ውስጥ ከመቀጠራቸው በፊት ስራ ያልነበራቸው በመሆናቸው በመቀጠራቸው ገቢ ለማግኘት ችለዋል። ነገር ግን ሰራተኞቹ እንደሚናገሩት የሚያገኙት ገቢ የዕለት ተዕለት ወጪያቸውን በተገቢ መልኩ አይሸፍንላቸውም።

ጥቂት ፋብሪካዎች ከወርሃዊ ደመወዝ ውጪ ያሉ ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ለሠራተኞቻቸው ያቀርባሉ:: ከነዚህም ውስጥ የምግብ፣ የማበረታቻ ክፍያ እንዲሁም የመጓጓዣ ወጪን መሸፈን የተጠቀሱ ናቸው። የተወሰኑት ፋብሪካዎች ከኮቪድ-19 ቫይረስ ወረርሽኝ ጋር ተያይዞ ባጋጠመው የገቢ መቀነስ ምክንያት እነዚህን ጥቅማ ጥቅሞች አቋርጠዋል። ከነዚህ ጥቅማ ጥቅሞች በተጨማሪ ሴት ሠራተኞች የተለያዩ ስልጠናዎችን ያገኛሉ:: በተለይም ሴቶቹ በሥራ ገበታቸው ላይ

እያሉ የልብስ ስፌት ስልጠና የማግኘት እድል ይመቻችላቸዋል። ይህም በተለይ ለሴት ሠራተኞች ጠቃሚነቱ የጎላ ነዉ።

በጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት ፋብሪካ ውስጥ የሚሰሩ ሴቶች ብዙ ተግዳሮቶች ይገጥሟቸዋል። ሴቶቹ ሪፖርት ያደረጓቸው ፆታዊ ጥቃቶች ቁጥር አነስተኛ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት አንድም የፋብሪካ አመራሮች እንደሚሉት ፆታዊ ጥቃት የሚፈፅሙ ግለሰቦች ላይ የማያዳግም ቅጣት ስለሚጣልባቸው ሊሆን ይችላል አልያም የተወሰኑት ቁልፍ ሰጪዎች እንዳሉት ፆታዊ ጥቃት ሲፈፀምባቸው ሴቶቹ በተለያዩ ምክንያቶች ችግሩን ለበላዮቻቸው አያሳውቁም።

ለመጓጓዣ የሚከፍሉት ከፍተኛ ክፍያ እና መፀዳጃ ቤት እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው ውስን ሰአት መሆኑ ሌሎች ሴት ሰራተኞች የሚገጥሟቸው ተግዳሮቶች ናቸው። እነዚህ ተግዳሮቶች ሠራተኞቹ ጤናቸውን እንዲሁም ምርታማነታቸውን እንደሚፈታተኑት ይናገራሉ። በተጨማሪም ሴቶች ወደ ቤታቸው ሲሄዱም የቤት ሥራ እንዲሰሩ ማህበረሰቡ ስለሚጠብቅባቸው ከፋብሪካ ሥራቸው በተጨማሪ የማብሰል፣ የማፅዳት እንዲሁም ቤተሰባቸውን የመንከባከብ ሚናቸው በፋብሪካ ውስጥ ያላቸውን ሥራ በትክክል እንዳይሰሩ በዛም ምክንያት የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን እንዲያጡ ያደርጋቸዋል።በተጨማሪም በቤት የተጣሉባቸው ኃላፊነቶች ፋብሪካ በሚሰሩ ሴቶች ላይ ቀላል የማይባል ጫና ይፈጥርባቸዋል።

በአጠቃላይ ሲታይ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ፋብሪካዎች ውስጥ የሚሰሩ ሴቶች በአመራር ቦታዎች ላይ አይገኙም። ብዙዎቹ የአመራር ሚና ያላቸው ሴቶች ከመስመር ተቆጣጣሪነት የሥራ መደብ ሲያልፉ አይታይም። በተጨማሪም በሠራተኛ ማሕበራት ውስጥ የአመራር ቦታ ላይ ስለማይገኙ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል ባሉ ድርድሮች ላይ ተፅዕኖዋቸው ውስን ነው። ለጥናቱ መረጃ በተሰበሰበባቸው ፋብሪካዎች ደግሞ የሠራተኛ ማህበራት ከነአካቴው ባለመኖራቸው ምክንያት የሠራተኛና አሠሪ ድርድሮች አይታወቁም።

## የፖሊሲ ምላሾች

በኢትዮጵያ በፋብሪካ ውስጥ የሚሰሩ ሴቶችን ሁኔታ ለማሻሻል ያለሙ ብዛት ያላቸው የህግ እና ፖሊሲ ሰነዶች ይገኛሉ። ለምሳሌ የትምህርት እና የጤና ፖሊሲዎች ሴት ሠራተኞች ወደ ትምህርት እንዲሄዱ በማበረታታት እና አጠቃላይ የጤና ሽፋን እንዲያገኙ በግልጽ አስቀምጧል። የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁም እንዲሁ የሴት ሠራተኞችን የስራ ሁኔታ ለማሻሻል ያለሙና በቁጥር በዛ ያሉ አንቀፆችን ይይዛል። ከአንቀፆቹ ውስጥ የስራ ሁኔታ መቆጣጠርን፣ የሰራተኛ ማህበራትን ማቋቋምን እንዲሁም አነስተኛ ደመወዝን የሚመለከቱ ይገኙበታል። ነገር ግን ፖሊሲዎችን ለማስፈፀም ከመንግስት በኩል ባለ የአቅም እና ቁርጠኝነት ማነስ ምክንያት ወደ ተግባር ሲተረጎሙ እና አላማቸው በተገቢው ደረጃ ሲሳካ አይታዩም።

## መደምደሚያ

በጨርቃ-ጨርቅና አልባሳት ሴክተር ውስጥ ብዙ ሴቶች ተቀጥረው ይገኛሉ። ይህ ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘውን ከፍተኛ የሥራ አጥ ቁጥር ለመቀነስ ጉልህ ሚና ይኖረዋል። ነገር ግን በሴክተሩ ተቀጥረ የሚሰሩ ሴቶች በህይወታቸው ውስጥ እርባና ያለው ለውጥ እንዲያመጡ ለማስቻል ከተፈለገ ሴቶቹ በስራ ቦታ የሚገጥሟቸውን ችግሮች የስርዓተ-ፆታ ፍላጎቶችን ባገናዘበ መልኩ መፍታት ያስፈልጋል። የሴት ሰራተኞችን የስራ ሁኔታ በማሻሻል ረገድ በተለይም መንግስት እና ፋብሪካዎቹ ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይገባል።

## የጥናቱ ምክረ-ሃሳቦች

### 1. የሠራተኛ ማህበራት እንዲቋቋሙ ድጋፍ ማድረግ እና ለሚቋቋሙት ማህበራትን ማገዝ

ምንም እንኳን የሠራተኛ ማህበራት የሠራተኞችን መብት ለማስጠበቅ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ቢሆንም በጨርቃ-ጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚሰሩ ሴት ሠራተኞች በማህበራት አልተደራጁም።። በመሆኑም በየኢንድስትሪዎቹ ሠራተኛ ማህበራት መቋቋም ያለባቸው ሲሆን የሚቋቋሙትም ማህበራት የሰራተኞች የሥራ ሁኔታ እንዲሻሻል ብሎም ኢንድስትሪው ውስጥ የተሻለ የስራ ግንኙነት እንዲሰፍን ከአሠሪዎቻቸው ጋር መደራደር መቻል አለባቸው። የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽንም የሠራተኛ ማህበራት በየኢንዱስትሪዎቹ እንዲቋቋሙ የማስተባበር ግዴታውን ሊወጣ ይገባዋል። በተጨማሪም ኮንፌዴሬሽኑ ለማህበር አባላት የሠራተኛ

መብትን ለማስጠበቅ የሚረዱ ስልጠናዎችን ሊያዘጋጅ ይገባል።

**2. መዋቅሮችን ማጠናከር፡-** በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ ስርአተ-ፆታ ላይ አተኩረው የሚሰሩ ጽ/ቤቶች በፋብሪካዎች ውስጥ የሚሰሩ የሴት ሠራተኞችን ሁኔታ በተሻለ መልኩ እንዲከታተሉ በገንዘብ እና በሰው አቅም መጠናከር አለባቸው። በተጨማሪም በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ ደረጃም ቢሆን ስረዓተ-ፆታ ላይ አትኩረው የሚሰሩ ተወካዮች ተመልምለው ከሥርዓተ-ፆታ ጋር የተገናኙና በየጊዜው የሚታቀዱ ፕሮግራሞችን እንዲያስተባብሩ ሊደረግ ይገባል።

### 3. የሠራተኞች ደህንነትና ጤንነትን ለመጠበቅ የተደነገጉ ደንቦችን ማስፈፀም

በመካከለኛ አልባሳት ኢንተርራይዝ የሚሰሩ ሴት ሠራተኞች ያለው የስራ ሁኔታ ደህንነታችውን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ነው። ምንም እንኳን የኢትዮጵያ መንግስት የሥራ ደህንነትን የመቆጣጠር ሥራን ባልተማከለ መልኩ በክ/ከተማ አልያም በወረዳ ደረጃ እንዲሰራ ለማድርግ አቅጣጫ ያስቀመጠ ቢሆንም፤ ከታች ያሉት የመንግስት አደረጃጀቶች በቂ የሰው ኃይል እና ሌሎች ግብዓቶች የሚያንሳቸው በመሆኑ የጨርቃ-ጨርቅና አልባሳት ኢንተርፐራይዞቹ በቂ ክትትልና ቁጥጥር አይደረግባቸውም። ስለሆነም ላሉት አደራጃጀቶች የሚያስፈልጋቸውን ግብዓት በማሟላት የሠራተኛ ደህንነትን ለማስጠበቅ የተደነገጉ ደንቦችን እንዲተገበሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

### 4. አነስተኛ ደመወዝን መወሰን እና ለሠራተኞች የመኖሪያ ቦታ ማመቻቸት

እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ2011 በታወጀው የኢትዮጵያ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ላይ በተመለከተው መሠረት የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስትር ከሠራተኞች፤ ከቀጣሪዎች፤ ከሠራተኛ ማህበራት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመስራት የደመወዝ ቦርድ እንዲቋቋም ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል። በተጨማሪም፣ በአዲስ ኢንዱስትሪ መንደር የሚገኙ ፋብሪካዎች የሴት ሠራተኞቻቸውን የመኖርያ ቤት ችግር ለመቅረፍ የመኖሪያ ቦታ የማመቻቸት ሥራ ሊሠሩ ይገባል።

### 5. የሴት ሠራተኞን አቅም መገንባት

መንግስት ከሲቪክ ማህበራት ጋር በመተባበር የሠራተኞች መብቶችን በተመለከተ ስልጠናዎችን፣ ውይይቶችን እንዲሁም የልምድ ልውውጦችን ቢያዘጋጅ በሴክተሩ ያሉ የተጠቀሱት ችግሮችን ለመቅረፍ ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በተጨማሪም ሴት ሠራተኞች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁ እና ሌሎች ተዛማጅ ህጎች ዙርያ ያላቸዉን ግንዛቤ በማጎልበት ሴቶች መብታቸውን እንዲጠይቁ የማስቻል ሥራ መስራት አስፈላጊ ነው።

**ፍሬህይወት ስንታሁ**
**እና**
**ክቡር እንግዳወርቅ**

ምንጭ፡- The State and Transformation of Female Wage Labour in Ethiopia: Lessons from the Textile/ Garment, Floriculture and Hospitality Industries. Ezana Amdework and Belete Bizuneh (Ed).

ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ ሠነድ የታተመው ከኦፕን ሶሳይቲ ኢንሽየቲቭ (ኦሶኢ) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው:: ለሠነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የተመራማሪዎቹ ሲሆን በምንም ሁኔታ የለጋሽ ድርጅቱን ወይም ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስን አቋም እንደሚያንጸባርቅ ተደርጎ መወሰድ የለበትም::

አድራሻ፡- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS) ፖ.ሣ.ቁ.፡- 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ፡- 0111545605/06 ፋክስ፡- 0111545608 ኢ.ሜል፡- fss@ethionet.et ድረ-ገጽ፡- www.fssethiopia.org